# የሕዝብ ተወካዮች አፈ ጉባዔ አቶ አባዱላ ገመዳ የሥራ መልቀቂያ አስገቡ

ሰበር ዜና ፖለቲካ
የሕዝብ ተወካዮች አፈ ጉባዔ አቶ አባዱላ ገመዳ የሥራ መልቀቂያ አስገቡ

7 October 2017



በጋዜጣዉ ሪፓርተር
የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባዔ አቶ አባዱላ ገመዳ ባልተጠበቀ ሁኔታ የሥራቸውን መልቀቂያ ለኢህአዴግ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አስገቡ፡፡

አቶ አባዱላ መልቀቂያውን ለኢህአዴግ አስፈጻሚ ኮሚቴ የዛሬ 15 ቀን አካባቢ ያስገቡ ሲሆን አስፈጻሚ ኮሚቴውም መልቀቂያቸውን ተቀብሏቸዋል፡፡

ለፓርላማው በጣም ቅርብ የሆኑ ምንጮች ለሪፖርተር እንዳረጋገጡት አፈ ጉባዔው መልቀቂያውን ካስገቡ በኋላ እስከትናንት ድረስ በሥራ ገበታቸው ላይ የነበሩ ሲሆን የፓርላማው የአመቱ የሥራ ዘመን መክፈቻው ላይ ሰኞ መስከረም 29 ቀን 2010 ዓ.ም. እንደሚኖሩ ታውቋል፡፡

በፓርላማው አሠራርና ሥነ ምግባር ደንብ መሰረት መልቀቂያው ለፓርላማው ምልዓተ ጉባዔ ይቀርብና ኢህአዴግ ለፓርላማው የሚያቀርበው እጩ በቦታው ይሾማል፡፡